EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የባሕል መድኃኒቶች ምዝገባና ሀገራዊ ጠቀሜታ

ባሕላዊ መድኃኒት በሽታን ለማከም ወይም ለመከላከል ተብሎ በኅብረተሰቡ ጥቅም ላይ የሚውል በባሕላዊ መንገድ ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት አካል እና ከማዕድናት የሚዘጋጁ መድኃኒቶችን የሚያጠቃልል ነው።

ይህ የሕክምና አይነት ዘመናዊ ሕክምና ጨርሶ ባልታወቀባት ዓለማችን ከአምስት ሺህ ዓመታት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረና የሰውን ልጅ ከተለያዩ ደዌዎች ሲታደግ የነበረ ባለውለታ ተደርጎ ይቆጠራል። በኢትዮጵያም ጥንት አባቶቻችን ከቀላል ስብራት ጀምሮ እስከ ካንሰር በሽታዎችን በማከም ኅብረተሰቡ ከባሕል ሕክምና መፍትሔ እንዲያገኝ ሲሠሩ ኖረዋል። ዛሬም ቢሆን ታዲያ የዘመናዊ ሕክምና አቅርቦት ተደራሽ ያለመሆን እንዲሁም ውድ በመሆኑ የተነሳ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ሰዎች አማራጫቸውን ወደ ባሕል መድኃኒት እንዲያዞሩ እንዳደረገ ይታመናል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ የተለያየ ባሕልና የአኗኗር ዘይቤ ያላቸው ማኅበረሰቦች ያሉባት በመሆኗ ለባሐል መድኃኒቶች ምቹ ከሆኑት ሀገሮች አንዱ አድርጓታል። እያንዳንዱ ማኅበረሰብ የራሱ የሆነ የባሕል መድኃኒት አሠራር ሒደት ያለው መሆኑ፣ የሀገሪቱ ተፈጥሯዊ አቀማመጥና በውስጡ ያሉ ብዝሐ ሕይወት (ባዮዳይቨርሲቲ)፣ በሀገሪቱ ብቻ የሚገኙ እንስሳትና ዕፅዋት መኖር ለባሕል መድኃኒት ምቹነት ተጠቃሾች ናቸው።

ሀገራችን በተለይ በተፈጥሮ ካላት ልዩ ልዩ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥና የአየር ንብረት ሳቢያ በዓለም ከሚገኙ የዕፅዋትና የእንስሳት ዝርያዎች አብዛኞዎቹን በመያዝ ትታወቃለች። ይህም ለጥንታዊ የባሕል ሕክምና መሠረት የሆኑ በርካታ ሀገር በቀል ዛፎችንና የመድኃኒት ዕፅዋት ዝርያዎች ባለቤት ለመሆን አብቅቷታል። ቀደምት ኢትዮጵያውያንም በእነዚህ የዕፅዋት ዝርያዎች፣ በእንስሳትና በልዩ ልዩ ማዕድናት ላይ እንደ ዘመናቸው የሥልጣኔ ደረጃ ምርምር በማድረግ ለዛሬው ትውልድ የደረሱና ለሚቀጥለው ትውልድ ሊተላለፉ የሚገቡ በርካታ መድኃኒቶችን ቀምመዋል። እየቀመሙም ነው።

ይሁንና በሀገራችን የባሕል ሕክምና አዋቂዎች ከአያቶቻቸውና ከቅድመ አያቶቻቸው ይዘው የመጡትን ዕውቀት የሚስተላልፉት ልጅ ካላቸው ለልጃቸው አሊያም በጣም ለሚወዱት ሰው ነው ሙያውን የሚያወርሱት። ያለበለዚያ ሲሞቱ ሙያው አብሮአቸው ይሞታል። ይህ ደግሞ ሙያው እንዳያድግና የተሻለ ደረጃ ላይ እንዳይደርስ አድርጎታል።

በየገዳማቱ፣ በየቤተክርስቲያናቱና በየመስጊዱ ውስጥ ተፅፈው የተቀመጡ የባሕል ሕክምናዎች አሉ። እነዚያን አውጥቶና አጥንቶ በግልጽ ኅብረተሰቡ እንዲጠቀምበት እምብዛም ስላልተደረገ ሕክምናው እየላላ፣ የመረሳትና የመጥፋት ሁኔታዎች እየታዩ መምጣታቸው ይነገራል።

ከዚህ ጎን ለጎን ዘርፉ እንዳያድግ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ባለፉት ዘመናት የሀገር በቀሉን የመድኃኒት ሕክምና ጥበብ አዋቂዎቹ በኅብረተሰቡ ዘንድ የነበራቸው ቦታና ክብር ዝቅተኛ በመሆኑ «ስር ማሽ» «ቅጠል በጣሽ» በሚል አንገት በሚያስደፉ ሸውራራ አተያይ፣ ከጥቁር አስማትና መጥፎ መናፍስት ጋር አያይዞ መመልከት የተለመደ በመሆኑ የባሕል መድኃኒትን አዋቂዎች እንዳይበዙና ዘርፉ እንዳያድግ እንቅፋት ሆኖ መቆየቱ ይታወቃል።

በአንፃሩ ዛሬ ደግሞ እውነተኛ የባሕል መድኃኒት አዋቂን ከሐሰተኛ የሚለዩ ወይም ዕውቅና የሚሰጡ ተቋማት ያልተጠናከሩ በመሆናቸው የተነሳ ሙያውን ለገንዘብ ማግኛ ብቻ ሲሉ ችሎታ ሳይኖራቸው የባሕል መድኃኒት አዋቂዎች ነን የሚሉትን በየመንደሩ እንደ አሸን የፈሉትን ሕገ ወጦች ለመቆጣጠርና በእግረኛ መንገድ መተላለፊያ ላይ አንጥፈው የባሕል መድኃኒት የሚቸረችሩትን መስመር ለማስያዝ አለመቻሉ ተጨማሪ ተግዳሮት ሆኖ ይጠቀሳል።

የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን የባሕል መድኃኒት እንደ ዘመናዊ ወይም ሳይንሳዊ መድኃኒት ሁሉ ደህንነት፣ ጥራትና ፈዋሽነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የባሕል መድኃኒቶች መመዝገብ የሚያስችል አሠራር ለመዘርጋት በአሁን ወቅት ረቂቅ ሕግ አዘጋጅቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር ያደረገ ይገኛል። ይህ ሕጉ ፀድቆ ሲወጣ ባሕላዊ መድኃኒቶችን በመመዝገብ አገሪቱ ያላትን ዕምቅ የባሕላዊ መድኃኒት ሀብት በአግባቡ ለመጠቀምና ዘርፉን ለመምራት ያስችላል ተብሎ ይጠበቃል።

የባሕል ሕክምና መድኃኒቶችን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል የምርምር ተቋማት ከማምረቻ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት እንዲሠሩ የሚጠበቅ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ምርቶቹ ከወጡ በኋላ ተፈላጊ የሆኑ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን አረጋግጦ ገበያ ውስጥ እንዲገቡ ፈቃድ የሚሰጥ ይሆናል። ይህም ተግባር በዋናነት በኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን በኩል የሚከናወን ነው።

ይህ ባሕላዊ መድኃኒት መዝግቦ ገበያ ላይ እንዲወጡ የማድረግ ሥርዓት በተለይም በአሁን ወቅት ከባሕላዊ መድኃኒት ዝግጅትና አጠቃቀም ጋር በተያያዘ በጉልህ የሚስተዋሉ የመድኃኒት መጠን (Dosage)፣ የአዘገጃጀት፣ የቁጥጥር ስልት፣መድኃኒቱ ከተወደሰ በኋላ ሊከተል የሚችለው ሁኔታ አለመታወቅና የመድኃኒቱ ንጽሕና የመሳሰሉት ችግሮች እንዲስተካከሉ መንገድ የሚከፍት ይሆናል።

የባሕላዊ መድኃኒቶች ማሳደግ በሀገሪቱ የጤና ፖሊሲ ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶ የተካተተ ቢሆንም ዘርፉ ያለበትን ማነቆዎች ተገንዝቦ ችግሮቹን ደረጃ በደረጃ የመፍታት ሥራ ጊዜ የማይሰጠውና ኅብረተሰቡን፣ መንግሥትንም ሆነ ሀገርን ሊጠቅም የሚችል ትልቅ ተግባር በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶት በአግባቡ ሊሠራበት ይገባል።

ሌሎች ሀገራት ከባሕል መድኃኒት ሕክምና እጅግ ከፍተኛ ገንዘብ እያገኙ ነው። ለምሳሌ ጀርመን በዓመት በመቶ ሚሊዮኖች ዩሮ ከባሕል መድኃኒት ገቢ ታገኛለች። ከአፍሪካም ደቡብ አፍሪካና ሞሪሺየስ ግንባር ቀደም ተጠቃሾች ናቸው።

ይሁንና ኢትዮጵያ ካላት ዕምቅ የተፈጥሮ ሀብትና የባሕል መድኃኒት አዋቂዎች አንፃር በሚፈለገው መልክ ጥቅም ማግኘት አልቻለችም። በመሆኑም ይህን ዕድል በስፋት ለመጠቀም የሚያስችል ሁኔታ ማመቻቸት፣ ሙያው ለትውልድ እንዲተላለፍ ማስተማር፣ በጽሑፍ ማቆየትና የተጀመረውን ዘርፉን በሕግ ማዕቀፍ ውስጥ የማስገባት ሥራን አጠናክሮ መቀጠል ለነገ የማይባል ሥራ ነው።

ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትም ከተቋቋሙበት ዓላማ አንፃር የባሕላዊ መድኃኒት ሕክምና ሙያን በዘመናዊ መንገድ ለማሳደግና ባለሙያዎችም ሙያቸውን ለትውልድ እንዲያስተላልፉ ዘርፉ ላይ ጥልቅ የምርምር ሥራዎችን መሥራት ይጠበቅባቸዋል። የሙያው አዋቂዎችም ሀገሪቱ ከዘርፉ ባላት ዕምቅ አቅም ልክ እንድትጠቀም፣ ራሳቸውም ሙያቸውን እንዲያሳድጉና መብታቸውን ለማስጠበቅ በተበጣጠሰ መልኩ ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ ይልቅ በአንድ ጠንካራ ሙያ ማኅበር ጥላ ስር ተደራጅተው ሀገራቸውና ሕዝባቸው የሚጠብቁባቸውን ኃላፊነት በመወጣት የሙያውን ክብር ከፍ ሊያደርጉ ይገባል።

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482
http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ